# የወሲባዊ እና አካላዊ ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ሰዎች የኢሚግሬሽን እና የቪዛ መረጃ

ስለ ኢሚግሬሽን እና የቪዛ ሁኔታቸው ጥያቄዎች ያሏቸው የውጭ ሃገር ተማሪዎች እና ምሁራን የኢሚግሬሽን ጠበቃ እርዳታ እንዲጠይቁ ይመከራሉ። ይህ ሰነድ አንዳንድ የሕግ ገጽታዎችን በተመለከተ ለማብራራት የቀረበ ሲሆን፣ ህጋዊ የምክር አገልግሎትን የሚተካ አይደለም።

**የጥቃት ሰለባ ነበርኩኝ። የኢሚግሬሽን ሁኔታዬ በካምፓስ ውስጥ ያሉ የተለያዩ አገልግሎቶችን የመጠቀም ሁኔታዬን ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል?**

አይኖረውም። በሕጉ መሰረት፣ የወሲብ ወይም የአካላዊ ጥቃት ሰለባዎች ወይም ከእነዚህ ጥቃቶች የተረፉ ተማሪዎች እና ሰራተኞች የኢሚግሬሽን እና የቪዛ ሁኔታቸው ምንም ይሁን ምን፣ በ1972 የትምህርት ማሻሻያ አንቀጽ (Title IX) እና በሴቶች ላይ ስለሚፈጸም ጥቃት አዋጅ (VAWA) መሰረት ለማንኛውም አይነት አገልግሎቶች ከሌሎች እኩል መብት አላቸው።

የካምፓስ ውስጥ የሕክምና እና የምክር አገልግሎቶችን እንዲሁም ስለሚኖሩ አቅርቦቶች በተመለከተ መረጃ በሚከተለው ድህረ ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል፥ https://1is2many.okstate.edu/

የተማሪን የስነ ምግባር ግምገማ ሂደት በተመለከተ መረጃ በሚከተለው ድህረ ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል፥ https://studentconduct.okstate.edu/code

ኮሌጁ ወንጀልን ሪፖርት ማድረግዎን መሠረት አድርጎ የበቀል ቅጣት ወይም ከሌሎች በተለየ መልኩ ሊመለከትዎት አይችልም።

**የተመዘገበ ወይም ያልተመዘገበ ስደተኛ ሆኜ ሳለ የወንጀል ክስ መመስረት እችላለሁ?**

አዎ። በእርስዎ ሁኔታ ላይ ስላለ ሰው የወሲብ ጥቃት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ በፍቅር ጓደኛ የሚደርስ ጥቃት፣ አድብቶ መከታተል ያሉትን የወንጀል ትርጓሜዎች የተመለከተ መረጃ በዓመታዊ የደህንነት ዘገባ ላይ ሊገኝ ይችላል፥ https://police.okstate.edu/annual-security-reports

ክስ መመስረትን በተመለከተ ዝርዝር ጥያቄዎች በሚከተለው አድራሻ ሊልኩ ይችላሉ፥

Oklahoma State University Police Department, OSUPD
104 USDA Building, Stillwater, Oklahoma 74078
405-564-6523
https://police.okstate.edu/
1is2many@okstate.edu

**ለወንጀል ተጎጂዎች የተለዩ የቪዛ እና የኢሚግሬሽን ሁኔታዎች አሉ?**

አዎ። የወሲብ ጥቃት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ በፍቅር ጓደኛ የሚደርስ ጥቃት፣ አድብቶ በመከታተል የሚደርስ ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ሰዎች U እና T ቪዛዎችን ጨምሮ ሌሎች የቪዛ አማራጮች ሊኖሩ ይችላሉ። ዝርዝር ሁኔታዎችን ለማግኘት፣ የኢሚግሬሽን ጠበቃን ማነጋገር ይችላሉ።

| U ቪዛ | T ቪዛ |
|---|---|
| ወሲባዊ ጥቃት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ አስገድዶ መድፈር፣ ድብደባ፣ ወይም ሌሎች ተዛማጅ ወንጀሎችን ጨምሮ በአንዳንድ የወንጀል ተግባር ምክንያት ከባድ አካላዊ ወይም አእምሯዊ ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ሰዎች፤<br>- ሰለባ የሆነው ሰው/ አመልካቹ የተዘረዘሩት የወንጀል ጥቃቶች መስፈርት የሚያሟላ መሆን ያለበት ሲሆን በወንጀል ምርመራ እና/ ወይም ክስ እንቅስቃሴ ላይ ማገዝ የሚችል መሆን መቻል አለበት<br>- በአጠቃላይ ለአራት ዓመታት ያክል የሚያገለግል ነው<br>- ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የኢሚግሬሽን ጠበቃን ያማክሩ፤ በተጨማሪም የሚከተለውን ድህረ ገጽ ይመልከቱ፥ | በሰዎች ህገ ወጥ ዝውውር ሰለባ ለሆኑ ሰዎች<br>- ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ድርጊት (ቶች) ለመመርመር ወይም በክስ ወቅት ከሕግ አስከባሪዎች ለቀረቡ ተገቢ ጥያቄዎች መተባበር መቻል (በአካላዊ ወይም በስነ ልቦናዊ መረበሽ ምክንያት መተባበር ካልቻሉ በስተቀር)፣ እና ተጠቂው/ አመልካቹ ከአሜሪካ እንዲወጣ ከተደረገ በጣም ከባድ የሆነ መከራ እንደሚደርስበት ማሳየት መቻል አለበት።<br>- በአጠቃላይ ለአራት ዓመታት ያክል የሚያገለግል ነው<br>- ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የኢሚግሬሽን ጠበቃን ያማክሩ፤ በተጨማሪም የሚከተለውን ድህረ ገጽ ይመልከቱ፥ |
| http://www.uscis.gov/humanitarian/victims-human-trafficking-other-crimes/victims-criminal-activity-u-nonimmigrant-status/victims-criminal-activity-u-nonimmigrant-status | http://www.uscis.gov/humanitarian/victims-human-trafficking-other-crimes/victims-human-trafficking-t-nonimmigrant-status |

**ተጨማሪ መረጃ ሊሰጠኝ የሚችል ቢሮ በካምፓስ ውስጥ አለ?**

, International Students & Scholars
250 Student Union, Stillwater, OK 74078
405-744-5459
https://lcl.okstate.edu/iss/
su-iss@okstate.edu

የውጭ ሃገር ተማሪዎች እና ምሁራን አገልግሎቶች ቢሮ የስደተኝነት ሁኔታን በተመለከተ ጠቃሚ መረጃ ሊሰጥ ይችላል። ሌሎች የቪዛ ሁኔታ ለውጦችን፣ ወይም ከመደበኛ F-1 እና J-1 የተማሪ ቪዛዎች፣ ወይም በቀጣሪ ስፖንሰር የተደረገ የስራ ቪዛ ህጋዊ አማራጮችን በተመለከተ ጥያቄዎች ካለዎት በሙያው ብቁ የሆነ የኢሚግሬሽን ጠበቃ ማማከር እንዳለብዎት ልብ ይበሉ።

| የቪዛ አማራጮች |
|---|

The State University of New York

| ቪዛቸው F-1 እና J-1 የሆኑ ተማሪዎች | H-1B, O-1, E-3, ወይም TN ሠራተኞች |
| --- | --- |
| • ፈቃድ ባለው የሕክምና ዶክተር፣ በኦስቶፓዚ ዶክተር ወይም ፈቃድ ባለው የስነልቦና ባለሙያ በተረጋገጠ የህክምና ሁኔታ ምክንያት የተቃለለ የትምህርት ኮርስ ቅናሽ አማራጮች<br>• የትምህርት ፕሮግራምዎትን የማቋረጥ አማራጮች እና ተያይዘው ሊመጡ የሚችሉ ነገሮች<br>• ተማሪው የትምህርት ፕሮግራሙን ለማቋረጥ ከመረጠ፣ በሌላ ጊዜ ወደ ትምህርት ፕሮግራሙ መመለስን በተመለከተ መረጃ<br>• የትዳር አጋርን በተመለከተ ያሉ አማራጮች እና ተያይዘው ሊመጡ የሚችሉ ነገሮች<br>• የቪዛ ሁኔታን በመለወጥ ዙሪያ ባሉ አማራጮች ላይ አጠቃላይ መረጃ።<br>• U እና T ቪዛዎችን በተመለከተ አጠቃላይ መረጃ። (ብቃት ወዳለው የኢሚግሬሽን ጠበቃ ማመልከት ወይም ሪፈር ማድረግ)<br>• ብቃት ወዳለው ጠበቃ ማመልከት ወይም ሪፈር ማድረግ | • ከስራ የመቅረት ፈቃድ አማራጮች እና ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢሚግሬሽን ሁኔታዎት ላይ ሊመጡ የሚችሉ ነገሮች<br>• የትዳር አጋርን በተመለከተ ያሉ አማራጮች እና ተያይዘው ሊመጡ የሚችሉ ነገሮች<br>• የቪዛ ሁኔታን በመለወጥ ዙሪያ ባሉ አማራጮች ላይ አጠቃላይ መረጃ። ብቃት ወዳለው የኢሚግሬሽን ጠበቃ ሪፈር ማድረግ።<br>• U እና T ቪዛዎችን በተመለከተ አጠቃላይ መረጃ። (ብቃት ወዳለው የኢሚግሬሽን ጠበቃ ማመልከት ወይም ሪፈር ማድረግ)<br>• ብቃት ወዳለው የኢሚግሬሽን ጠበቃ ማመልከት ወይም ሪፈር ማድረግ<br>• በይደር ላይ ያለ የአሜሪካ ቋሚ መኖሪያ (ተቀባይነት ገና ያላገኘ ግሪን ካርድ)<br>• ስራዎትን መልቀቅዎ በቀጣሪዎት ስፖንሰር የተደረገ እና ውሳኔው በይደር ላይ ያለ የቋሚ መኖሪያ ፍቃድ ማመልከቻ ላይ የሚኖረው ተጽእኖ፣<br>• ብቃት ወዳለው ጠበቃ ማመልከት ወይም ሪፈር ማድረግ |

**የኢሚግሬሽን ጠበቃ ማለት ምን ማለት ነው፣ የሚሰራው ስራስ ምንድን ነው?**

የኢሚግሬሽን ጠበቆች በኢሚግሬሽን ህግ ዘርፍ ዙሪያ ብቃት ያላቸው እና ፍቃድ ያላቸው ጠበቆች ናቸው። ለደምበኞች ጥብቅና በመቆም ያገለግላሉ፣ እንዲሁም በኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት እና ለኢሚግሬሽን ጥቅሞች ማመልከቻ በመሙላት ሂደት በኢሚግሬሽን መስሪያ ቤቶች ዘንድ ሊወክሏቸው ይችላሉ። ጠበቃው አጠቃላይ ምክር መስጠት እና የኢሚግሬሽን አማራጮችን በማንሳት ለመወያየት ይችላል። እንደማንኛውም ጠበቃ፣ የኢሚግሬሽን ጠበቆች በሙያዊ ስነ ምግባር እና በህጋዊ መስፈርቶች የሚገዙ ሲሆን ከደምበኞች ጋር የሚደረግን ማንኛውንም ውይይት በምስጢ ይጠብቃሉ።

**የአካባቢውን የኢሚግሬሽን ጠበቃ ማግኘት የምችለው የት ነው?**

የአሜሪካ ዜግነት እና ኢሚግሬሽን አገልግሎቶች (USCIS)፣ የሃገር ደህንነት መምሪያ (DHS) ቢሮ ግለሰቦች በነጻ ወይም በአነስተኛ ዋጋ የሕግ-ነክ ውክልና እንዲያገኙ ለማገዝ ሁለት ድህረ-ገጾች አዘጋጅቷል፥

USCIS: በእርስዎ ማህበረሰብ ድህረ-ገጽ ላይ እርዳታ ያግኙ

USCIS: የህጋዊ አገልግሎቶች ድህረ-ገጽ ያግኙ

የስደተኞች የይግባኝ ቦርድ (BIA) በነጻ ወይም በዝቅተኛ ወጪ የኢሚግሬሽን አገልግሎት የሚሰጡ ጠበቆች ዝርዝር በየእስቴቱ ዘርዝሮ ያቀርባል።

የአሜሪካ የኢሚግሬሽብ የሕግ ባለሞያዎች ማኅበር (AILA) ተማሪዎችን ወይም ምሁራንን የኢሚግሬሽን ጠበቃ ማግኘት እንዲችሉ ለማገዝ የሚያስችል የኦንላይን የኢሚግሬሽን ጠበቃ የጥቆማ አገልግሎት ይሰጣል።

በተጨማሪም የአሜሪካ ጠበቃዎች ማኅበር ደግሞ በየእስቴቱ የህግ አገልግሎቶች በማግኘት ዙሪያ መረጃ ይሰጣል።